ታላቁ ተጋድሎ

የ13ኛ ትምህርት መምሪያ

የትምህርቱ መሪ ጥቅስ፤ ራዕይ 21:3-4

የትምህርቱ ዋና ሐሳቦች

ይህንን ስ13 ሳምንታት የዘለቀ ትምህርት ስንጀምር በሰማይ የተጀመረው ታላቁ ውዝግብ ለዘላለም የሚቀጥል ሳይሆን ማብቂያ ያለው ጦርነት መሆኑን ጠቅሰን ነበር። ላለፉት 12 ሳምንታት ውዝግቡ በተለያዩ የታሪክ እጥፋቶች እንዴት እንደቀጠለ የተማርን ሲሆን በዚህ 13ኛ ትምህርት ደግሞ እንዴት እንደሚጠናቀቅ እናጠናለን። ውዝግቡ ወደ መጠናቀቅ ሲመጣ የሚከሰቱት ወሳኝ ኩነቶች የሚከተሉት ናቸው፤

1. ታላቁ የመከራ ዘመን
2. የክርስቶስ ዳግም ወደ ምድር መመለስ
3. ሺህ ዓመትና ፍርድ በሰማይ (ይህ የሞድረንም የሚጠቀልል ነው)
4. የሁሉም ነገር መታደስና ሕይወት እንደገና ለዘላለም መቀጠል ናቸው።

ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ እንደገለጽነው ይህ ታላቅ ውዝግብ ዘላለማዊ ሆኖ የማይቀጥል፣ አቻ ባልሆኑ ኀይላት መካከል የሚደረግና ሲጠናቀቅም በእግዚአብሔር አሸናፊነት የሚደመደም ነው። ይህ ለእኛ በምድር ሆነን በውዝግቡ ውስጥ ተሳታፊ ስለሆንነው ለሁን የሚደርስብንን የሕይወት መከራና ስቃይ በተስፋና በእምነት እንድናልፍ መጽናናትና መደፋፈር የሚሰጠን ነው። በዚሁ ሁሉ ውስጥ በእግዚአብሔር ልንታመን፣ በቃሉ ልንመሠረት፣ በእምነት ልንጸና በተስፋ ደስ ሊለን እና ሌሎችን ወደዚህ አስደናቂ ሕይወት ልንመራ ይገባናል። በዚህ ሳምንት ጥናታችን የሚከተሉትን 4 ነጥቦች በዋነኛነት እንማራለን፦

1. **ታላቁ ውዝግብ ወደ መጠናቀቂያው ሲቃረብ ከሚከሰተው ታላቅ የመከራ ዘመን እግዚአብሔር ራሱ ጥበቃና ከለላ ይሆነናል።**
2. **ውዝግቡ ሲጠናቀቅ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ምክንያት በሰይጣን፣ በሥጋና በንጢአት ላይ የምናገኘው የሦስትዮሽ ድል እውን ይሆናል።**
3. **የእግዚአብሔር ድል የእኛ ድል ይሆናል፤ ይህንንም በእምነት የምንቀበለው ነው።**
4. **ታላቁ ውዝግብ በአምላካችን አሸናፊነት ሲጠናቀቅና የምድር ጉዳይ ለዘላለም ተወስኖ ሲያበቃ ጌታችን ዳግም ይመጣል፣ የሙታን ትንሣኤ ይሆናል፣ ሺህ ዓመት በሰማይ "ዳኝነት" ይሰጠናል (ራዕ 20:4)፤ ምድር ትታደሳለች፣ ዘላለማዊ ሕይወት ይጀምራል።**

13ኛ ትምህርት፤ የምድር ታሪክ መዝጊያ ክስተቶች

1. ተስፋ በመከራ ዘመን፤

- **ጌታችን በክብር ዳግም ወደዚህ ምድር ከመመለሱ በፊት ምን ይከሰታል? (ዳን 12:1-2፤ ኤር 30:7፤ ራዕ 22:11-12)**
- **ከክርስቶስ ዳግም መመለስ በፊት ለሚሆነው ታላቁ የመከራ ዘመን እንዴት ነው መዘጋጀት የምንችለው? (1ዮሐ 3:1-3፤ ዮሐ 10:27-29)**
- **በዚህ አስጨናቂ የመከራ ወቅት እግዚአብሔር እንደሚታደገን መጽሐፍ ቅዱስ ምን ተስፋ ይሰጠናል? (መዝ 50:15፤ 27:5፤ 91:1-11)**

2. የጌታችን በክብር የመመለስ ተስፋ፤

- **ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱና ለኛ የሰጠን ተስፋ ምንድነው? (ዮሐ 14:1-3)**
- **ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ በክብር መመለስ ለቲቶ ምን አለው? (ቲቶ 2:11-14)**
- **በእነዚህ ጥቅሶች ስለ ተስፋና ተስፋ ስለ መቁረጥ ምን እንማራለን? (ኢሳ 25:8-9፤ ራዕይ 6:14-17)**
- **ወደዚህች ምድር ጌታችን በክብር ሲመለስ ምን አስደናቂ ክስተት ይሆናል? (1ተሰ 4:13-17፤ 1ቆሮ 15:51-53)**
- **ክርስቶስ በግርማው ሲመለስ የዳኑት ምን ብለው ይዘምራሉ? (ራዕ 15:2-4)**

3. ሺህ ዓመት፤

- **ጌታችን በክብር ከተመለሰ በኋላ ሰይጣንና አጋንንቱ ለእንድ ሺህ ዓመት የት ነው የሚታሰሩት? (ራዕይ 20:1-3፤ ማነጻጸሪያ ዘፍ 1:2)**
- **በሺህ ዓመት ገዜ ምድር ምን እንደምትመስል ነቢያት ምን ይላሉ? (ኤር 4: 23-26፤ 25:33፤ ኢሳ 24:1፤3፤5)**
- **በሺህ ዓመት ገዜ ውስጥ የዳኑት በሰማይ ምን ያደርጋሉ? (ራዕይ 20:4፤6)**
- **የሰው ሁሉ ጉዳይ የተጠናቀቀ ቢሆንም "ዳኝነት የሚሰጠን" በምን ላይ ፍርድ እንድንሰጥ ነው? (ራዕይ 20:4)**
- **ሺህ ዓመት ሲጠናቀቅ ምን ይሆናል? (ራዕይ 20:7-9)**
- **ንጥአን የተኮነኑ ከሆነ ተመልሶ ለመሞት ለምን ወደ ሕይወት ይመጣሉ? (ሮሜ 14:10-11፤ ራዕይ 20:11-15)**

4. ዘላለማዊ ሕይወት ወይም ዘላለማዊ ሞት!

- **የዳኑት ምን ዓይነት ክብር ነው የሚጠብቃቸው? (ዮሐ 3:16፤ 14:23፤ ራዕይ 21:1-4፤ 22:1-5)**
- **በዓመጻቸው የጸኑትን የሚጠብቃቸው በዘላለም እሳት እየተቃጠሉ መኖር ነው ወይስ ምንድነው? (ራዕይ 20:9፤ ሚል 4:1-3፤ መዝ 37:20)**
- **በሰማይ ተጀምሮ ወደ ምድር በዘለቀውና በርካታ ሺህ ዓመታትንባሰቆጠረው ታላቅ ውዝግብ እግዚአብሔር ፍቅር መሆኑን እንዴት ማስረዳት ይቻላል?**